# ብ አ ዴ ን (አ ዴ ፓ) የተባለ ጥላሸት

እስከ መቼ ድረስ ይህንን እምቦጭ የአማራ ሕዝብ ሊሸከመው ይችላል። በስር ነቀል የታጀበ ስብሰባ አድርጌ ራሴን አስተካክዬላሁ እያለ ከብት ባልዋለበት ኩበት ለቀማ የወጣው ይህ እኩይ ፀረ አማራ ስብስብ አሁንም በከፍተኛ አመራሩ ላይ አማራ ያልሆኑ፤ አንዲትም ቀን ስለአማራው ሰቆቃ ያልጮሁ ግን በያጋጣሚው አማራውን ለኦነግ መሰል አክራሪዎች አሳልፈው ሲሰጡ የነበሩ ሰዎችን ከየትም ለቃቅሞ አማራው ላይ ፈላጭ ቆራጭ እንዲሆኑ ባደባባይ ጭኖባታል። የሕወሐት ካድሬዎች አሁንም ውስጡ አሉበት። ከቀበሌ አንስቶ ባህርዳር ድረስ በነዚሁ የአማራውን ጥቅሞች አሳልፈው ለሌላ በሚሰጡ ተኩላዎች ክልሉን ሰንቆ ይዞ ተሻሽያለሁ ይለናል። አማራው በነቂስ ከታች እስከ ላይ ተንቀሳቅሶ እነ እከሌ ይወገዱልኝ ሲል ያደረገውን ተጋድሎ በመፍራት ብቻ ተጠይ ግለሰቦችን ገሸሽ ያደረገ ቢመስልም ውስጥ ውስጡን ግን እነዚሁ ነፍስ በላዎች በፌደራል ስልጣን ተብነሽንሽው አሁንም አሉ። አለምነው መኮንን እኮ በሚኒስትር ማዕረግ የ'መለስ' አካዳሚ ሀላፊ ነው። ሰሜን ሸዋን ለትግሬዎች ሲገብር የኖረው ወያኔው ግርማ የሺጥላ የፌዴሬሽን ምክር ቤት የአማራ ተወካይ አባል ሆንዋል። ተካ ቱሉ የተባለውም የኦነግ አሽባሪ እስከ ቅርብ ግዜ የብ አ ዴ ን የስራ አስፈጻሚ አባል የነበረ በሚኒስትር ደዔታ ማዕረግ የአለምነው ምክትል ነው። እነዚህን በምሳሌነት ባቀርብም ሌሎች በርካታ በትምህርት ሰበብ ተነስተዋል እየተባለ በአዲስ አበባ በስልጣን ተንበሽብሸዋል። ለመሆኑ ወያኔ በአማራው በኩል በደረሰበት መተፋትና ተቃውሞ ተወጥሮ እያለ ብ አ ዴ ን ከጎኑ ሆነው ሲገሉና ሲያስገድሉ የነበሩትን ካድሬዎች ያባርራል ብላችሁ ትገምታላችሁ?

በምክር ቤቱም ስብሰባ በሕዝብ የተጠሉና እንዲነሱ ትግል ሲካሄድባቸው የነበሩትን ካድሬዎች የቢሮ ሀላፊ አድርጎ የሾመ ዓይን አውጣ ድርጅት ነው። ለምሳሌ ፈንታ ደጀንን ማቅረብ ይቻላል። እሺ መቼ ይሆን በአማራ ባጀት የሚመራው የክልሉ ሲቪል ሰርቪስ ከፍተኛ ሀላፊዎች ትግሬዎችና ኦሮሞ ሆነው የሚቀጥሉት? አማራው የተማረ ሰው ጠፍቶበታል? ልዑል ዮህንስ የተባለው ትግሬ ሕወሐት ሶስት ዓመት ሙሉ የባህልና ቱሪዝም ቢሮ አድራጊ ፈጣሪ ምክትል ሀላፊ ሆኖ በታሪካዊ ላሊበላ ቅርስ ከፍተኛ ውድመት ሲፈጠር ምን የተሰራ ነበረ? ዛሬ ዶ/ር አብይ የባህልና ቱሪዝም ሚኒስትር ያደረጋት የአማራ ምሁር ባህርዳር ሆና ልዑል ያዛት እንደነበርም እየታወቀ አዴፓ ተለውጫለሁ ሲል ሀፍረት አይሰማውም? የአማራ ድምፅ ሆነ እየተባለ የሚዘገብለትስ የአማራ መገናኛ ብዙሀንን የሚያስተዳድረው የክልሉ ኮሚዩኒኬሽን ቢሮ ምክትል ሀላፊ ሕሊና መብርሀቱ አይደለችም? ቅልጥ ያለች ጠባብ ትግሬና የወያኔ ካድሬ። ለዛውም የተሾመችው እነ ደመቀ የአማራ ፓርቲ ሆነናል ባሉ ማግስት። ሌሎችንም በዝርዝር ማቅረብ ይቻላል፡ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ማለቴ ነው።

አንድ በጣም ደስ ብሎኝ የነበረው በመፈንቅለ መንግስት ሴራ ተውንጅለው ታስረው የተፈቱት ብርጋዴር ጀነራል አሳምነው ፅጌ የክልሉን የጸጥታ ቢሮ እንዲመሩ መሾማቸው ነበር። እርሳቸውም በአማራ ቲቪ ላይ የአዴፓ አመራር በመሆናቸው በጋራም ሆነ በተናጠል የአማራውን ብሔረተኝነት የሚያጠናክር ስራ ከመስራት አልቦዝንም ብለው ነበር። ግን በወልቃይትና በተለይም በራያ የአማራ ማንነት ትግል የሰው ህይወት ሲጠፋና እንዲያውም ይለይላችሁ ተብሎ የመከላከያ ሰራዊት ከመቀሌ ትላንትናና ዛሬ ተነስቶ ራያ ቆቦ ላይ ሕዝብ እያሸበረ ባለብት ወቅት እርሳቸው የት ነው ያሉት? ምን

ይሄ ብቻ ገንዳውህ አካባቢ በወያኔ የታጠቁና ልባቸው ያበጠባቸው ቅማንት ነን የሚሉ ፀረ አማራ የሆኑ ቡድኖች ሰላማዊ አማራዎችን በጠራራ ፀሀይ ሲገድሉና ሲያዋክቡ ጀነራሉ መሾማቸው ምን ያመጣው ለውጥ አለ? ነገሩ ሁሉ ውሀ ቅዳ ውሀ መልስ ሆንዋል። ብቻ!ጀነራሉ አይፈረድባቸውም! ምንም ቢሆን እስራትንና በደልን የቀመሱ በመሆናቸው ለአማራው የማንነት ተጋድሎ መቃናት ድጋፍ በግላቸው ይኖራቸዋል ተብሎ ስለሚገመት ባስቸኳዋይ በአማራ ፖሊስና ልዩ ሀይል የተሰገሰጉትን የሕወሐት አገልጋዮችን ከያዙዋቸው ስልጣኖች እንዲያስነሱዋቸው ልናሳስባቸው የግድ ይለናል። ግን ይሰሙን ይሆን? መቼም ጉድና ጭራ ከበስተሁዋላ ነው ይባላልና የምናየው ይሆናል።

በቅርቡ ዶር አህመድ በሰባት ቢሊዮን ዶላር ይሰራሉ ብለው ካቀረቡዋቸው ፕሮጀክቶች ውስጥ አብዛኛው አሁንም በትግራይና በኦሮሚያ የሚከናወኑ መሆናቸው ያደባባይ ሚስጥር ሆኖ ሳለ ከንግዲህ ወዲያ በየክልሉ የፌደራል መንግስት ሲያሰራ በሚያቅዳቸው ላይ ጠንካራ የሆነ ተሳትፎ አድርገን የአማራ ክልል እኩል ተካፋይና ተጠቃሚ እንዲሆን እንታገላለን ያሉን እነ ደመቀ ዛሬ ላይ የገቡትን ቃል ረስተውት የቀድሞውን የተለመደ አሽከርነትና ተላላኪነት ሚና መጫወትን የሙጥኝ ብለው ተያይዘውታል። እሺ ይሰራሉ በተባሉ የመተማና ጨሞጋ የሀይል ማመንጫ ብቻ ተወስነናል፡ ለመሆኑ እነዚህስ ተግባራዊ ይሆናሉ ብላችሁ አዴፓን ታምናላችሁ? ጥናቱ አለቀለት ተብሎ ለአስር ዓመት ሲነገርለት የነበረው የደብረ ብርሀን የነፋስ ሀይል ማመንጫስ ጉዳይ ድብስብስ ብሎ ሲጠፋ እነገዱና አዴፓ ለምን ዝም አሉ? የቱጋ ነው የተለወጡት? እነዚህ ሰዎች የሚመሩት የአዴፓ ጽ/ት ቤት ባለባት ባህርዳር ሀያ ሰባት ዓመት ሙሉ በአባይ ወንዝ ላይ ድልድይ ማሰራትና የጢስ አባይን መንገድ አስፋልት ማስለበስ ያቃታቸው አይደሉምን? ስለ አዴፓ ከዚህ የበለጠ ምን የሚያሳፍር ነገር ይኖራል? ለነገሩም በሚሊዮን የሚቆጠር ማስረጃ ይዘን የአዴፓን አልጫነት ማሳየት ይቻለናል። ለምሳሌ ከሰበታ እስከ ጅቡቲ የተዘረጋው የባቡር መስመር በምንጃርና ሸንኮራ ወረዳ ውስጥ አልፎ ይሄዳል። ባቡሩ በሚያልፍባቸው የኦሮሞ መንደሮች ሳይቀር ጣቢያዎች ተገንብተዋል፤ ለዛውም በጣም ውበት የተላበሱ ዘመናዊ ግንባታዎች ናቸው። እዩት እንግዲህ የአዴፓን ጥንካሬ። የአማራው ሰሜን ሸዋ ግን ባቡሩንና ድምጹን ማየትና መስማት ብቻ እንጂ ጣቢያ ስላልተሰራላቸው ተጠቃሚ ሳይሆኑ ቀርተዋል ይህ ደግሞ የአዴፓ ልፍስፍስ አመራር በምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ደመቀና በክልሉ ፕሬዝዳንት ገዱ ተወጥሮ የፖለቲካ ማዕከል ስልጣን ለሚይዘው ሀይል ተንበርክኮ ማሸርገድ ላይ እንጂ ስለ አማራው ዕኩል ተጠቃሚነት ቦታ ስለማይሰጠው ነው።

አዴፓ የአማራውን አንጡራ መሬቶች አሁንም በነኦነግ ማስወረሩን አጠናክሮ ቀጥሎበታል። ከወሎና ከሸዋ አራት ወረዳዎችን ቆርሶ የኦሮሚያ ልዩ ዞን ብሎ ሲመሰረት የክልሉ ሕገ መንግስት እያለ በክልሉ ከ 93 በመቶ በላይ የሆነውን አማራ ሳያማክር በወያኔ በተሰጠው የባንዳነት ስልጣን ዓይኑን ጨፍኖና እጁን ታጥቦ ልዩ ዞኖች የመንገንጠል ስልጣን አላቸው በሚል የአጥፍቶ ጠፊ የመጃጃል ባዶ ወኔ ላይ ተወጥሮ አማራውን አሳልፎ ሽጦታል። አስተማሪዎችን ከወለጋና አርሲ ወዘተ. በራሱ ባጀት እየቀጠረ አስመጥቶ ላለፉት ሀያ አራትና ሀያ አምስት ዓመቶች ኦሮሚኛ(ኦሮሚፋ) በአማርኛ ላይ የበላይነት ያለው እንዲሆን አድርጎዋል። ዛሬ ደግሞ አማራ የሆነና ከቅም ቅም ሲወርድ ሲዋረድ ተፈጥሮ ከሚኖርበት ቦታ በኦነግ ቄሮዎች ይገደላል፤ ይባረራል፤ ይፈናቀላል፤ በራሱ አማርኛ መማርም ሆነ የአስተዳደር ጉዳዮችን

ማከናወን በአገሩ ተነፍጎ ይገኛል። በተጨማሪም የኦነግ ባንዲራ የሚውለበለብበት፤ ኦሮሞነት የገነነበት፤ አማራነት በጠላትነት የተፈረጀበት ዞን ሆንዋል። ብ አ ዴ ን አዴፓ ውስጥ ውስጡን ዞኑን አሳልፎ ለኦነግ ቄሮዎች ሸልሞታል። ወልቃይትን፤ ጠገዴን፤ ጠለምትን፤ መተከልና ራያን እንደዚሁም አዲስ አበባ በረራን የአማራ ናቸው ለማለት ድፍረት ያጣ ልፍስፍስ ስብስብ ነው።እንግዲህ እነ ደመቀና ገዱ ከነድርጅታቸው በአማራው ላይ የተጫኑ የጥፋት ተልዕኮ ያነገቡ መልዕክተኞችና ጥላሸት ናቸው ቢባል ስህተት ላይሆን ይችላል። ለዚህም ነበር በድርጅቱ ውስጥ ያሉ አማራዎች ከጫፍ እስከ ጫፍ በአማራ ብሔረተኝነት ጎን እንዲቆሙ ጥሪዎች ከግራና ቀኝ ሲቀርብላቸው የሰነበተው። ለነዚህ ወገኖች ዛሬም ሆነ ነጋ የሚያዋጣው አማራን ሆኖ መገኘት ብቻ ነው።

አብነት ሁነኛው ነኝ!